# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 18: ምህረቷ አንቺ ነሽ?

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት RETURNS TO SCHOOL**

- **ሰብለ (F, 50)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **አልማዝ (F, 16)**

**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት  AND ቅዱስ TALK**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት  (F, 40)**

**SCENE 3: አልማዝ MEETS “THE” ምህረት**

- **አልማዝ (F, 16)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 4: ምህረት AND NIKI ARE REINTRODUCED TO CLASS**

- **STUDENT (M, 15)**
- **በለጠ (M, 16)**
- **እየሩስ (F, 15)**

- **ሰብለ (F, 50)**
- **5 – 8 CLASS STUDENTS (M/F)**

## <u>INTRO</u>

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ "መዘዙን መቀበል"የተሰኘዉ ሁለተኛ ዙርድራማ ነዉ። መቼም የወጣት አፍሪቃዉያኑ ታሪክ ምን ደረጃ ላይ ደረሰ ብላችሁጓጉታችኋል!አይደለም እንዴ? ንጉሴ እጽ በመውሰዱ ከትምህርት ቤት ቢባረርም ትምህርት ቤቱ እንዲመለስ ሁለተኛ እድል ሰጥቶታል፡፡ የክፍል ጓደኛው ምህረትም የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እርግዝናዋን በማወቃቸው ተባራ ነበር፡፡ ሆኖም በቅርቡ ምህረት ለእናቷ አስደሳች ወሬ ነግራቸዋለለች፡፡**

## 2. EPISODE 16, LINES 109 – 110:

<u>ምህረት</u>**:** ርዕሰ መምህርት ሰብለ ደብዳቤ ጻፈችልኝ፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ መስፈርት ካሟላሁ ብቻ ተመልሼ እንድገባ ፈቅዶልኛል፡፡

<u>ወ/ሮ ሉሊት</u> **:** የእኔ ልጅ ይሄ ድንቅ የምስራች ነው!

## 3. NARRATOR:

**የምህረት የክፍል ጓደኛ ዳንኤል የመጣው ከጎረቤት ሀገር ላቦሪያ ነው፡፡ ያልተወለደው ልጇ አባት ሲሆን፤ እርሱም ከትምህርት ቤት ተባሮ ነበር፡፡ በዳንኤል ህይወት ውስጥ ያለችው ሴት ግን ምህረት ብቻአትመስልም…በልውውጥ የትምርት መረሃ-ግብር ከላቦሪያ ቦንጎ አካዳሚ ለትምህርት የመጣችዋ ተማሪ አልማዝም አለችበት፤ ቦንጎ አካዳሚ እንደደረሰች ዳንኤልን ምን እንዳጋጠመው ለማወቅ በጣም ጓጉታለች፡፡**

***KW BEGIN***

## 4. EPISODE 15, LINES 65 – 69:

<u>አልማዝ:</u> እም-ርዕሰ መምህርት ሰብለ የሆነ ነገር ልጠይቅ እችላለሁ? (…)ዳንኤል ካሳሁን ን ያዉቁታል?

<u>ሰብለ</u>: አዎ፣ በርግጥ አዉቀዋለሁ፣ ዳንኤል ካባረርናቸው ተማሪዎች መካከል አንዱ ነው፣

<u>አልማዝ</u>: ምን? ለምን?

***KW END***

## 5. NARRATOR:

በዛሬው፣ “ምህረቷ አንቺ ነሽ?” ከተሰኘው ክፍል አስገራሚ ሁኔታዎችን ታደምጣላችሁ፡፡ ድራማዉ የሚጀምረዉ በቦንጎ አካዳሚ ርዕሠ-መምህርቷ ቢሮ ውስጥ ሳለን ነዉ፡፡ ዕለቱ ለምህረት የተለየ ቀን ነው…

## <u>SCENE 1: ምህረት RETURNS TO SCHOOL</u>

## 6. ATMO: ሰብለ OFFICE ATMO, DURING SCHOOL TIME

**7. ሰብለ:** ተቀመጪ፣ ምህረት፡፡

## 8. SFX: CHAIR PULLED

**9. ምህረት:** **(Acts out sitting heavily)**

**10. ሰብለ:** ወደ ቦንጎ አካዳሚ በድጋሚ እንኳን በደህን መጣሽ፡፡.

**11.** ምህረት: አመሰግናለሁ ርዕሰ መምህርት ሰብለ። ዳግም በመመለሴ በእውነት ተደስቻለሁ!

***KW BEGIN***

**12.** ሰብለ: እስኪ ንገሪኝ እንዴት አሳለፍሽው? እርግዝናሽስ እንዴት ነው?

**13.** ምህረት: **(shyly)** ደህና ነኝ እትዬ ሰብለ።

**14.** ሰብለ: እስከዛሬ በቂ ምግብ አግኝተሻል? እንደማይሽበጣም ከስተሻል፣ እጆችሽ፣ ፊትሽ...ያው ከሆድሽ በስተቀር ሁሉም ነገር።

**15.** ምህረት: አበላሁ እትዬ ሠብለ። አመሰግናለሁ።

***KW END***

**16.** ሰብለ: **(takes a stricter tone)** ምህረት እንደምታውቂው እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ መቆየት የምትፈልጊ ከሆነ መፈጸም የሚገቡሽ የተወሰኑ መስፈርቶች አሉ።

**17.** ምህረት: የሚሉኝን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ፣ እትዬ ሰብለ።

***KW BEGIN***

**18.** ሰብለ: በመጀመሪያ ነገር ለዚህ መዘጋጀትሽን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

**19.** ምህረት: አዎ ዝግጁ ነኝ!

**20.** ሰብለ: እውነቱን ለመናገር፤ የተማሪ ጓደኞችሽን ትችት እና ማመናጨቅ መቋቋም ይኖርብሻል፡፡ ያንጓጥጡሻል፡፡ በርግጥ ለማስቆም የቻልኩትን ያህል የምሞክር ቢሆንም ሁል ጊዜም መሀላችሁ እየተገኘሁ ያንን ማድረግ አልችልም፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ እራስሽን የጣልሽው አንቺው ስለሆንሽ የሚመጣውን ውጤት መጋፈጥ ያለብሽም አንቺው ነሽ፡፡ ለመቋቋም ተዘጋጅተሻል?

**21.** ምህረት: **(eagerly)** ምንም ቢሉ ጉዳዬ አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ግድ የሚሰጠኝ ትምህርቴ ብቻ ነው፡፡ እና ለልጄ ምሳሌ መሆን እፈልጋለሁ፡፡.

**22.** ሰብለ: የነበረሽን ታላቅ ጉጉት አለማጣትሽን ማየቴ አስደስቶኛል፡.

**23.** ምህረት: አመሰግናለሁ እትዬ ሠብለ፡፡

***KW END***

**24.** ሰብለ: አንዱ ጠቃሚ ቅድመ ሁኔታ ቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግሽ ነው፡፡ በእርግጥ ብዙውን ጊዜ እዚህ ይህን የማናደርግ ቢሆንም በዚህ ልዩ ሁኔታ ከትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ተነጋግረን ይህንን ልታመቻችልሽ ተስማምተናል፡፡ ቅድመ ወሊድ ክሊኒኮች ምን እንደሆኑ ታውቂያለሽ?

**25.** ምህረት: አዎ እትዬ ሠብለ፡፡ የወንድሜ ሀኪም እንደነገረችኝ እናት ለመሆን የተዘጋጁትን ለወሊድ እንዲዘጋጁ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

**26.** ሰብለ: ጥሩ፤ አሁን የህክምና ክትትልሽን በየትኛውም ምክንያት ብታቋርጪ ከትምህርት ቤት ትባረሪያለሽ፡፡ ገባሽ?

**27.** ምህረት: አዎ በደንብ ገብቶኛል እትዬ ሰብለ፡፡

**28.** ሰብለ: በተጨማሪም በሳምንት አንድ ጊዜ በወጣት ማዕከሉ የምክክር ክፍለ ጊዜ ትሳተፊያለሽ።.

**29.** ምህረት: እሺ መምህር።

***KW BEGIN***

**30.** ሰብለ: አሁን ይህ ሁሉ ከትምርትሽ በተጨማሪ ስለሆነ ብዙ ጊዜ እንደሚወስድ አዉቃለሁ ግን  የግድ ነው። እና እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ካልቻልሽ ሌላ እድል እንደማይሰጥሽ አትርሺ!

**31.** ምህረት: ገባኝ እትዬ ሰብለ። ቃል እገባሎታለሁ፣ አላሳፍሮትም።.

**32.** ሰብለ: አዩ። ይህን ቃል ከዚህ በፊትም ሰምቼው ነበር። እንደገና እንደማትረሺው ተስፋ እናድርግ! እና አሁን እንድትተዋወቂው የምፈልገው አንድ ሰው አለ።

.

***KW END***

**33. SFX: PICKS UP PHONE AND DIALS**

**34.** ሰብለ: ቀለሟ? እንድትገባ አሳያት።

**35. SFX: PHONE IS REPLACED**

**36. SFX: KNOCK ON THE DOOR**

**37.** ሰብለ: ግቢ፣ አልማዝ.

**38. SFX: DOOR OPENING**

**39.** አልማዝ: ደህና አደሩ፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ.

**40.** ሰብለ: ደህና አደርሽ፣ አልማዝ። ምህረት ትባላለች፣ ተዋወቂያት።.

**41.** ምህረት: **(friendly)** ሄሎ፣ ስለተዋወኩሽ ደስ ብሎኛል።.

**42.** አልማዝ: **(gasps)**

**43.** ሰብለ: ችግር አለ? አልማዝ!

**44.** አልማዝ: **(forces a cough)** የለም፣ እትዬ፣ እንደው ጉሮሮዬ ላይ የሆነ ነገር ገብቶ ነው ለ።

**45.** ሰብለ: ምህረት፣ ይህች አልማዝ ትባላለች፣ ከላቦራ የመጣች አዲስ የልውውጥ መረሃ-ግብር ተማሪያችን ናት።አልማዝ የእቻ ለእቻ ቡድን አማካሪ ስትሆን በወጣት ማዕከሉ የምክክር ጉዳይሽ ተጠሪ ትሆናለች።

**46.** አልማዝ: **(gasps again)**

**47.** ሰብለ: አሁን ሁለታችሁም ውጪ. ዛፉ ስር ተቀምጣችሁ ትንሽ ጊዜ ብትነጋገሩ የበለጠ ትተዋወቃላችሁ። በአስራ አምስት ደቂቃ ውስጥ መጥቼ እወስዳችኋለሁ። እሺ?

**48.** ምህረት/አልማዝ: እሺ፣ እትዬ.

**49.** ሰብለ: እባካችሁ ንጉሴን ግባ በሉልኝ። ውጪ እየጠበቀኝ መሆን አለበት።

**50.** ምህረት/አልማዝ: እሺ ፣ እትዬ ሠብለ።.

**51. MUSICAL INTERLUDE**

***KW BEGIN***

**<u>SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት AND ቅዱስ TALK</u>**

**52. ATMO: TANDIKA SLUMS, INSIDE ምህረት HUT**

**53. SFX: SOMEONE STIRRING BUBBLING PORRIDGE**

**54.** ቅዱስ: **(laughs to himself)** ለነገሩ አጥሚት ማብሰል ከባድ አይደለም። ከአሁን በኋላ እማዬን ወይም እህቴ ምህረትን አጥሚት እስኪያዘጋጁልኝ አልጠብቅም። ግን እናቴ ከመምጣቷ በፊት አጥቤ ብጨርስ ይሻላል። ከደረሰችብኝ…

**55. SFX: DOOR BURSTS OPEN, FOOTSTEPS**

**56.** ወ/ሮ ሉሊት : **(approaching)** ይቅርታ ቅዱስ ዘገየሁ አይደል … **(shouts)** ወይኔ አምላኬ! ምን እያደረግህ ነው? እያበሰልክ? ይህንን ምድጃ እንዳትነካ ነግሬህ አልነበር! ምን ነካህ? ይሄን የጥንቸል የመሰለ ጆሮ ይዘህም የምለዉ አይሰማህም?

**57.** ቅዱስ: **(scared)** ይቅርታ እማዬ። በጣም ርቦኝ ነበር!

**58.** ወ/ሮ ሉሊት : ቤቱን ልታቃጥለው ትችል ነበር እኮ!

**59.** ቅዱስ: **(silent)**

**60.** ወ/ሮ ሉሊት : መልስልኝ!

**61.** ቅዱስ: **(cries)** ይቅርታ እማዬ! ከእንግዲህ ወድያ ምንም ነገር አላበስልም፣ ቃል እገባልሻለሁ፡፡

**62.** ወ/ሮ ሉሊት : **(sighs)** ቅዱስዬ፣ ይቅርታ ጮህኩብህ፡፡ አንተ ማለት ጥሩ ልጅ እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ ግን እሳት ላይ ለመስራት ገና ህጻን ነህ፡፡ እሳት መጥፎ እና አደገኛ እንደሆነ መረዳት አለብህ፡፡ ያለንበትም የተጎሳቆለ እና ምንም አስተማማኝ ያልሆነ መንደር ነው፡፡ ቤቶቹ ተጠጋግተው የተሰሩ ናቸው! እዚህ እሳት ከተነሳ በምንም ማቆም ስለማይቻል ትልቅ ጥፋት የሚያደርስ ሲሆን የእኛን ቤት ብቻ ሳይሆን የጎረቤቶቻችንንም ያወድማል፡፡ ያ እንዲሆን ትፈልጋለህ?

**63.** ቅዱስ: **(sniffles)** አልፈልግም እማዬ፡፡

**64.** ወ/ሮ ሉሊት : **(breathes out loudly)** በጣም ዘግይቼ በመምጣቴ ይቅርታ፡፡ ግን ቤተሰቦቼ ትንሽ ምግብ የምገዛበት ገንዘብ ስለላኩልኝ ማውጣት ነበረብኝ፡፡ የሚቀጥለው ጊዜ፣ እኔን ጠብቅ እሺ?

**65.** ቅዱስ: **(meekly)** እሺ እማዬ፡፡

**66. SFX: PORRIDGE BEING STIRRED**

**67.** ወ/ሮ ሉሊት : አሁን አጥሚቱን ልስራልህ … **(laughs despite herself)** ወይየኔ ቅዱሴ…እንደእዚህ እኮ አይደለም የሚሰራዉ፡፡ ውሃ በዛ አድርገህ መጨመር አለብህ፣ አለበለዚያ ሙጫ ሙጫ ነዉ የሚለዉ

**68.** ቅዱስ: **(laughs shyly)**

**69. MUSICAL INTERLUDE**

***KW END***

**<u>SCENE 3: አልማዝ MEETS “THE” ምህረት</u>**

**70. SFX: BONGO ACADEMY, OUTSIDE, DURING SCHOOL TIME**

**71.** አልማዝ: **(mean)** እሺ ምህረቷ ማለት አንቺ ነሽ?

**72.** ምህረት: ምን ማለትሽ ነው?

**73.** አልማዝ: የወንድ ጓደኛዬን የወሰድሽብኝ ምህረቷአንቺ ነሽ! **(more to herself)** እና ወደ ትምህርት ቤት እንድትቀላቀይ አንቺን ላማክር እና ልረዳ ይታሰባል! አይመስለኝም!

**74.** ምህረት: ስለምን እያወራሽ እንደሆነ ልትነግሪኝ ትችያለሽ? ገና አሁን መገናኘታችን ነው! ምን … **(realizes)** ማድረግ… ቆይ -ይህ ነገር ስለ ዳንኤል ነው? **(disbelieving)** ዳንኤል የወንድ ጓደኛሽ ነው? አይሆንም! ዳንኤል ከእኔ በፊት የሴት ጓደኛ ኖሮት እንደማያውቅ ነግሮኛል!

**75.** አልማዝ: **(not believing her)** ነው! ልክ ነሽ፣ በጣም፣ እንጂ!

**76.** ምህረት: በእውነት! እኔ ብቻ የእርሱ እንደሆንኩ ነግሮኛል! **(starts crying)** ያለውን ሁሉ አምኜው ነበር እና አሁን እኔን እይኝ!

***KW BEGIN***

**77.** አልማዝ: ዳንኤል ለረጅም ጊዜ የወንድ ጓደኛዬ ነበር። ቤተሰቦቻችንም በጣም ይቀራረባሉ!

**78.** **ምህረት:** **(apologetic)** አዝናለሁ፣ አልማዝ። እኔ ይሄን አላውቅም ነበር።

**79.** **አልማዝ:** **(sighs)** ውሽታም!

**80.** **ምህረት:** እባክሽን እመኚኝ! አውቄ ቢሆን ኖሮ አንዳችም ነገር ከእርሱ ጋር አልጀምርም ነበር።.

***KW END***

**81.** **አልማዝ:** የወንድ ጓደኛዬን ነጥቀሽብኝ፣ እንዲባረር አደረገሽው በእዝያ ላይ አሁን ልጁን ሆድሽ ውስጥ ተሸክመሻል! ታስጠይኛለሽ፣ ምህረት!

**82.** **ምህረት:** **(desperate)** ግን እ…እ… እኔ ያን አላወቅኩም… እባክሽን ባላወቅሁት ነገር አትጥዪኝ! የአቻ ለአቻ አማካሪዬ እንምትሆኚም አትርሺ?

**83.** **አልማዝ:** **(sarcastic)** ልክ ነው ባክሽ! እንዴት ያለ አስደሳች ጊዜ ይኖረናል!

**84.** **ምህረት:** አልማዝ እባክሽን …

**85.** **አልማዝ:** **(coldly)** አሁን ከርዕሰ መምህርት ሰብለ ጋር ወደክፍል መግባት ይኖርብናል። እዛ ጋ ከንጉሤ ጋር በእጃቸዉ እየጠሩን ነው።

**86. SFX:** **አልማዝ GETTING UP AND WALKING AWAY**

**87.** **ምህረት:** **(sighs)**

**88. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: ምህረት AND NIKI ARE REINTRODUCED TO CLASS

**89. ATMO: CLASSROOM, INSIDE, DURING SCHOOL TIME**

***KW BEGIN***

**90. CLASS: NOISY CLASS, STUDENTS CHATTING, DRUMMING ON DESKS AS THEY SING ETC.**

**91. በለጠ:** ቀይ መብራት! እያንዳንድሽ ወደ ወንበርሽ! ርዕሰ መምህርቷ እየመጡ ናቸዉ! ምህረት እና ንጉሴም አብረዋቸዉ ናቸው!

**92. SFX: FOOTSTEPS AS THEY RUN TO THEIR PLACES**

**93. CLASS:** **(quietens down, but whispering: “**እሺ ምህረት እና ንጉሜ ተመለሱ ማለት ነው**?” / “**ግን እኔ ያረገዘች መስሎኝ ነበር እኮ**!” / “**እንዴ**!** ቆይ ዳንኤልስ**?” etc.)**

**94. SFX: PAGES TURNED AS STUDENTS PRETEND TO STUDY**

***KW END***

**95. SFX: ሰብለ’S HIGH-HEELED FOOTSTEPS ENTERING**

**96. ሰብለ:** **(sarcastically, to the class)** ኧረግ፣ ኧረግ፣ ኧረግ ሁላችሁም እንዴት በጥናት ተጠምዳችኋል ባካችሁ፤አይደል?

**97. CLASS:** **(serious)** ልክ ነው  መምህርት ሰብለ።

**98.** ሰብለ: በሉ አሁን ማስመሰላችሁን አቁሙ። ጫጫታችሁ እታች ድረስ ይሰማ ነበር። በለጠ የክፍል አለቃ እንደመሆንህ ከአሁን በኋላ ክፍሉ ጸጥታ የሰፈነበት እንዲሆን እፈልጋለሁ። ግልጽ ነው?

**99.** በለጠ: አዎ እትዬ ሰብለ.

**100.** ሰብለ: **(calls)** አልማዝ ሂጂና ተቀመጪ.. **(shout)** ንጉሴ፣ ምህረት፣ ኑ ግቡ።

**101. SFX: FOOTSTEPS (THREE PEOPLE)**

**102. SFX: DOOR CLOSING**

**103. CLASS IS SURPRISED, CHATTING**

(“ወይኔአምላኬ፣ እውነትም ነፍሰጡር ናት!”/ ”እና የሀሺሹ ጌታም መጥቷል!” /”ዳንኤል ግን የት አለ?” ወ.ዘ.ተ)

**104.** ሰብለ: ጸጥታ!

**105. PIN DROP SILENCE**

**106.** ሰብለ: ሁላችሁም እንደምታውቁት ምህረት እና ንጉሴ በስነ-ስርዓት ጉድለት ከትምህርት ቤት ተባረዉ ነበር።

**107. CLASS STARTS CHATTING AGAIN**

**108.** እየሩስ:**(cheekily)** የዳንኤል ሚስት !

**109.** **ሰብለ:** እየሩስ፣ በይ አሁን ይበቃሻል! ምህረት እና ንጉሴ ከዛሬ ጀምሮ ትምህርታቸዉን እንደገና ይጀምራሉ። ማክበር የሚገባቸው ጥብቅ ቅድመ ሁኔታዎች ግን አሉ፤ አለበለዚያ ከነአካቴውይሰናበቷታል!

**110. CLASS ERUPTS - TALKING, SIGHS, CHEEKY COMMENTS**

**111.** **ሰብለ: (talks over them)** አሁን ሁላችሁም አድምጡኝ። ስለ ምህረት ወይም ንጉሴ የማንኳጠጥ አይነት አስተያየት ስትሰጡ ባገኛችሁ፤ ውርድ ከእራሴ!.

**112. CLASS IS QUIET**

**113.** **ሰብለ:** በእነርሱ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ፤ ለሁላችሁም የማስጠንቀቂያ ደወል ነው። ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ነገር እንደገና ቢከሰት የስነ-ስርዓት ኮሚቴው እንደ አሁኑ አይራራም።.

**114. CLASS PROTESTS**

**115.** **ሰብለ:** ግልጽ የሆንኩላችሁ ይመስለኛል። ምህረት፣ ንጉሴ፣ መቀመጥ ትችላላችሁ.

**116. SFX: TWO PEOPLE’S FOOTSTEPS**

**117. SFX: CHAIRS SCRAPING AS THEY SIT DOWN**

## 118. OUTRO – NARRATOR:

**ይገርማል...ዛሬ በተለይ በምህረት እና አልማዝ ላይ ብዙ ነገር ተከስቷል! እነዚህ ሁለት ልጆች የልብ ጓደኞች የሚሆኑም አይመስልም...አልማዝ “ምህረቷን” ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ማግኘቷ ምን ስሜት እንዳሳደረባት ማወቅ ትፈልጋላችሁ? መልካም፤ እንግዲያውስ የዕለት ሁኔታዋን በምትቀርፅበት የቪዲዮ ዘገባዋ ላይ ያስቀመጠችዉን ድረ-ገጻችን ላይ ይከታተሉ። የድራማውን ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኛሉ። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገናኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**